# የአይጥ ምስክርነት—ከቃሊቲ ሲሰጥ

ከድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ
zeaddisu_gebeya@yahoo.com

ሰማህ ወይ ወዳጄ
የኔን ደባል ታሪክ
መጽሐፍ ፃፈ ሰማሁ
ከጠባቂው ከስልክ
አለማወቅ ክፉ
ጠፋኝ ገንዘብ ከባንክ
ወይ አለመታደል
ወይ አለመባረክ
ቶምቦላ አመለጠኝ
በሃዘን ልብረክረክ

ያንተ የኔ ደባሎች
በቅንጅት ሲያርሱ
የተቀሩት ጓዶች
በአንድነት ሲነሱ
የኔ ገራም ደባል
ታጅቦ በነሱ
ወረቀት ብዕሩን
ሸክፎ ከልብሱ
ሳየው ነበር ሲጭር
ሲናገር ከራሱ
ምንም ሳይረብሸው
ጩኸት ትርምሱ

ብታየው ወዳጄ
ሲጽፈው ሲጭረው
መለስ ቀለስ ብሎ
ወርውሮ ሲጥለው
ደግሞ ውዳቂውን
አምርሮ ሲያጠናው
በብዕሩ እየወጋ
በእጁ እያቀናው
ከፊቱ ደስታ
ፈገግታ እይቸረው
መፃፍ ብቻ መቼ
ጥበቃም ነበረው
ወራት ተቆጠሩ
መሰልቸት ሳይገባው
በጣሪያ ሁካታ
ጫጫታ ሳይገታው
ቁንጫ ቱሃኑ
ላፍታም ሳይበግረው
አቦ ሰው ጠንካራ
ይሄስ አንበሳ ነው
ደመኛ ጠላቱን
ድመቱን ይያዘው

እኔ ያጣጣልኳት
የዘብጥያ ወረቀት

ቢያሻኝ ልቀዳድድ
ልጥላት ልምራት
ለካስ ዕንቁ ኖራ
አይ መሃይምነት
ኮበለለች ከሃገር
በሃዘን በስሜት
ለሃገር አታሚዎች
ዕድል እንደሌላት
እጇን ሰጠች ገብታ
ከኡጋንዳ ለዕትመት
ሃገር ገባች ሰማሁ
በሚስጥር በብልሃት
ገበያዋ ጦፏል
ሰው ተራኮተባት

አንዱ ከመንግሥት ቤት
በብርሃን ይጭራል
ሲያሻው ዋቢ መጽሐፍ
ድህረ-ገጽም ያያል
ቪዲዮ ስልኩንም
ሺውንም ያዘምታል
ሌላው ከዘብጥያ
በሚስጥር ይከትባል
መጣጥፍ ሃሳቡን
ከደረቱ አቅፏል
በአይነ-ቁራኛ
ጠባቂ ይቃኛል

የመጽሐፉን ዱካ
ኮቴ ሊከተሉ
ጠባቂ ሰላዮች
ደህንነት በሙሉ
እርስ በራሳቸው
ይተራመሳሉ
ሚስጥሩን ለማውጣት
ሕዝቡን ያምሳሉ
የአይን ምስክሮች
ከጣሪያ እያሉ
የእንቆቅልሹን መልስ
ከሰው ልጅ ይሻሉ

ከመንግሥት ቤታችን
በድሎት ያደገች
ከሚስጥር ጽሑፏ
ትግልን ገጥማለች
ፍረድ ያገሬ ሰው
ሃይለኛዋ ማን ነች?
ድምጽህን ጠንቀቅ በል
አደጋ ሞልታለች

ፍርፋሪ ምግብ
ቅልውጥ ቢጣፍጥም
ደባል ጎረቤቴ
የራስ ዘር ቢያስጠላም
ሰው ይታሰር ከዚህ
ፀልዬም አላውቅም
ይሰንብትም ከዚህ
ፍፁም አልጠይቅም

የኖረ ሃሳቤ
ይኸው ፍላጎቴ
አሁን ተሸርሽሯል
ንዋይ በማየቴ
የለመደው እጁ
እንዲሆነኝ ሀብቴ

አመላልስ ገባሁ
ይህንን ካንደበቴ
ትንሽ ክረምልኝ
ደባል ጎረቤቴ
ይቅር በለኝ ጌታ
በክፉ ፀሎቴ

ብርሃን ሲነጋ
ጎህ ሲቀድም ልናይ
ድቅድቁ ጨለማ
ሊገፈፍ ከሰማይ
የጽልመቱን ዜና
መለስን እንዳናይ
ተዘከረን ጌታ
ጠብቀን ከዕኩይ

*************************

© ድሚልኝ ብህሬ-ዘአዲሱ ገበያ
ነሐሴ 1998
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
September 2006